# መሠረተ ሃይማኖት

## አንደኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

# መሠረተ ሃይማኖት አንደኛ ክፍል

## እግዚአብሔር መኖርና የፈጠራቸው ፍጥረት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ዓለም አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

# ማውጫ


አርእስት ገጽ

ምዕራፍ አንድ ............................................................ ፩

ነገረ እግዚአብሔር ...................................................... ፩

መግቢያ ................................................................. ፩

፩.፩ እግዚአብሔር ማን ነው ................................. ፪

፩.፪ አምላክ ስለ መሆኑ ........................................ ፫

፩.፫ የሁሉ ፈጣሪ ስለመሆኑ ................................. ፬

ምዕራፍ ሁለት ......................................................... ፲

ሥነ ፍጥረት ............................................................ ፲፪

፬.፩ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ስለመፍጠሩ ........... ፲፪

፬.፪ ከእሑድ እስከ አርብ ያሉ ፍጥረታት

(የፍጥረታቱን ዝርዝር በቁጥር ማሳወቅ) ............... ፲፪

፬.፫ የሰው ልጅ ክቡር ፍጥረት መሆኑ .................. ፲፰

ምዕራፍ ሦስት ......................................................... ፳፩

እግዚአብሔር መልካም ነገር ሁሉ የሚሰጠንና

ጸሎትን የሚሰማ ስለመሆኑ ........................................ ፳፩

፫፩ እግዚአብሔር መልካም ነገርን ይሰጠናል .......... ፳፩

፫.፪ እግዚአብሔር ጸሎትን ይሰማል ........................ ፳፫

፫.፫ ስለ ክፋትና እግዚአብሔር ከክፉ ነገር

የሚጠብቀን ስለመሆኑ ........................................ ፳፬

፫.፫.፩ የሰይጣን ክፋት .................................... ፳፬

# ማውጫ


**አርእስት** **ገጽ**

፫.፬ ሥላሴ የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ .......... ፴፮

ምዕራፍ አራት ........................................................ ፴፱

የእግዚአብሔር ባሕርይ ................................................ ፵

፬.፩ ቅዱስ ነው ........................................................ ፵

፬.፪ ሕያው ነው ...................................................... ፵

፬.፫ በሁሉ ቦታ አለ .............................................. ፵

፬.፬ ሰዎችን ሁሉ የሚወድ ነው ........................... ፵፩

፬.፭ ጸሎትን የሚሰማ ነው ................................... ፵፪

# ምዕራፍ አንድ
# ነገረ እግዚአብሔር

**የምዕራፉ ዓላማ**

ልጆች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፤

- ስለ እግዚአብሔር አምላክነት እና ፈጣሪነት ያውቃሉ።

**እግዚአብሔር ማለት**

- የዓለም ጌታ
- የሁሉ ፈጣሪ
- አስገኚ ማለት ነው።

## መግቢያ

ነገረ እግዚአብሔር ከሁለት ቃላት የተገኘ ጥምር ቃል ሲሆን፤ ነገር ማለት ትምህርት፣ የአንድ ነገር መገለጫ ማለት ነው። እግዚአብሔር ማለት ደግሞ የግእዝ ቃል ሲሆን፤ እርሱም የሁለት ቃላት ጥምረት ነው። እነርሱም እግዚእ እና ብሔር ሲሆኑ እግዚእ ማለት ጌታ ሲሆን፤ ብሔር ማለት ደግሞ ዓለም፣ ሀገር ማለት ነው።

## ፩. ፩ እግዚአብሔር ማን ነው?

ልጆች እግዚአብሔር የዓለም ሁሉ ጌታ ነው።

👉እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት የነበረ አሁንም ያለ ወደ ፊትም የሚኖር ነው። **"እግዚአብሔርም ሙሴን ፦ ያለና የሚኖር እኔ ነኝ አለው።"** (ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፲፬ ) **"ጌታ ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።"** (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፶፰)

👉እግዚአብሔር የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ የፈጠረ ነው። **"ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ (እግዚአብሔር) ነውና።"** (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፲፯ ቁጥር ፳፬)

👉እግዚአብሔር ያልፈጠረው ያላስገኘው ምንም ምን ፍጥረት የለም። **"ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው።"** (ትንቢት ኤርምያስ ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፲፪)

👉**"ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጧ ያለውን ያጸና፥ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ እስትንፋስን፥ ለሚሄዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል"** (ትንቢት ኢሳይያስ ምዕራፍ ፵፪ ቁጥር ፭)

## ፩. ፪ አምላክ ስለ መሆኑ

ልጆች አምላክ የሚለው ቃል ፈጣሪ እና ገዥ ማለት ሲሆን እግዚአብሔርም ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ መሆኑን ያስረዳል። ስለ አምላክነቱ የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ያስረዳሉ።

👉 **" በፀሐይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከኔ በቀር ሌላ አምላክ እንዳሌለ ያውቁ ዘንድ ከእኔም ሌላ አምላክ የለም።"** (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፵፭ ቁጥር ፮)

👉 **"የምድርም ነገሥታት ገዥ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።"** (የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፭)

ስለሆነም እግዚአብሔር አምላክ ነው። ለእርሱ መገዛት፣ እርሱን ብቻ ማምለክ፣ ለእርሱ መታዘዝ እንዲሁም እሺ ማለት ይገባናል።

## ፩. ፫ የሁሉ ፈጣሪ ስለ መሆኑ

ልጆች ፈጣሪ የሚለው ቃል ፈጠረ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አስገኚ፣ አምጪ፣ ሠሪ፣ አድራጊ ማለት ነው። ታድያ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ነው ስንልም የሁሉ አስገኚ፣ የሁሉ አምጪ፣ የሁሉ ሠሪ እና የሁሉ አድራጊ ነው ማለታችን ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ተገልጿል።

- **"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።"** (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፩)
- **"እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።"** (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፯)
- **"እርሱም ሰማይንና ምድርን ባሕርንም ፥ በእነርሱ ውስጥ ያለውንም ሁሉ የፈጠረ።"** (መዝሙረ ዳዊት መዝሙር ፻፵፮ ቁጥር ፮)

እግዚአብሔር በስድስት ቀን በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ፈጥሯል። በሰማይ መላእክትን፤ የምናያቸውን ከዋክብትን፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን፣ ደመናውን ሁሉ የፈጠረው እርሱ ነው። በምድር ያሉትን ሕይወት ያላቸውንና የሌላቸውን ፍጥረታትን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው።



ሥዕል ፩.፩፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው የሚታዩ ፍጥረታት

በምድር ያሉትን ሕይወት ያላቸውን ሰውን፣ እንስሳትን እና ዕፅዋትን እግዚአብሔር አስገኝቷል። በሰማይ የሚበሩ ፍጥረታትን የተለያየ ዓይነት ወፎችን በየዛፉ የሚንጠላጠሉትን እንደ ጦጣ ዝንጀሮ ያሉትን፣ በሆዳቸው የሚሳቡትን እንደ እባብ የመሰሉትን፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩትን (የሚሄዱትን) እንደ በሬ ላም አህያ ፈረስ ግመል አንበሳ ዝሆን ጅብ የመሳሰሉትን፣ አፈር ውስጥ የሚኖሩትን ትላትሎችን እና በአጉሊ መነጽር የሚታዩትን እጅግ በጣም ትናንሽ ፍጥረታትንም ፈጥሯል።



ሥዕል ፩.፪ ፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው የተለያዩ ዕፀዋት

እግዚአብሔር ለምግብነት፣ ለመድኃኒትነት እና ለመጠለያ መሥሪያነት የሚያገለግሉ ዕፀዋትንም ፈጥሯል። እነዚህ ዕፀዋት እንደላም በግ ፍየል ላሉት ምግብ እንደ ጦጣ እና አእዋፍ ላሉት መጠለያና ምግብ ለኛ ለሰዎች ደግሞ ምግብ፣ ቁሳቁስ እና ቤት መሥሪያ እንዲሁም መድኃኒት ሆነው ያገለግሉን ዘንድ እግዚአብሔር አዘጋጅቶልናልና ስለዚህ ፍቅሩም ልናመሰግነው ይገባናል። በጣም ረጃጅምና ወፋፍራም ከሆኑት ትላልቅ ዛፎች ጀምሮ አጫጭር፣ ቀጫጭን እና ለጥቂት ጊዜ እስከሚቆዩት ዕፀዋት ድረስ ሁሉንም ያስገኛቸው (የፈጠራቸው)

እግዚአብሔር እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሕይወት ያላቸው ሁሉ ብዙ እንዲሆኑ ፈቅዶ ፈጥሯቸዋል፡፡ “እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው፦ ብዙ፥ ተባዙም፥ የባሕርንም ውኃ ሙሉአት፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ፡፡” (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፪)

ከነዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸውን ፍጥረታት ፈጥሯል፡፡ እነርሱም በምድር ውኃን፣ መሬትን፣ አየርን፣ እሳትን፣ ድንጋዩን ያካትታሉ፡፡ በሰማይ ፀሐይ፣ ከዋክብትን፣ ጨረቃ መጥቀስ እንችላለን፡፡ እነዚህም ለሰው ልጅ ምግብና መጠጥ፣ መኖሪያ መስሪያ፣ አርሶ መብያ ቦታ፣ በታመመ ጊዜ መድኃኒት እንዲሆኑት ተፈጥረዋል፡፡ ሌሎች ሕይወት ያላቸውም ይጠቀሙባቸው ዘንድ እግዚአብሔር ፈጥሯቸዋል፡፡



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

**“ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው፡፡”**

**(ትንቢት ኤርምያስ ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፲፪)**

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ::

፩. እግዚአብሔር ማለት የዓለም ጌታ ማለት ነው::

፪. ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት በምድር ያሉ ሥነ ፍጥረት ናቸው::

፫.እግዚአብሔር በስድስት ቀን በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ ፈጥሯል::

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከተሰጡት አማራጭ መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

፩. እግዚአብሔር ማን ነው?

ሀ. አምላክ ነው:: ለ. ፈጣሪ ነው::

ሐ. ሁሉም መልስ ናቸው::

፪. እግዚአብሔር እፅዋትን ለሰዎች የፈጠረው ለምንድን ነው?

ሀ. መጠለያ እንዲሠሩበት ለ. ለምግብነት

ሐ. ሁሉም መልስ ናቸው::

# ምዕራፍ ሁለት
# ሥነ ፍጥረት

## የምዕራፉ ዓላማ


ልጆች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፤

- እግዚአብሔር በስድስት ቀን የፈጠራቸውን ፍጥረታት እነማን እንድሆኑ አውቀው በቃላቸው ይዘረዝራሉ::

## ቁልፍ ቃላት

- ነቢብ ፡ መናገር ማለት ነው::
- አርምሞ ፡ አለመናገር ማለት ነው::
- ገቢር ፡ መስራት ማለት ነው::

- ሥነ ማለት ያማረ፣ የተዋበ፣ የተወደደ፣ የተስማማ ማለት ነው:: ፍጥረት ማለት ደግሞ መፈጠር፣ መገኘት፣ መወለድ ማለት ነው:: ሥነ ፍጥረት ማለት ያማረ፣ የተዋበ የተወደደ ፍጥረት ማለት ነው::
- **"እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ"** (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፴፩)



ሥዕል ፪.፩ : እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረታት

## ፪.፩ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ስለ መፍጠሩ

እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ ፈጥሯል ‹‹እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይና ምድር ፈጠረ›› ብሎም ፍጥረታትን እንደፈጠረ ቅዱስ መጽሐፍ ነግሮናል። ይህም በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እና ሁለት እንዲሁም በሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሥነ ፍጥረትን በማጥናት የታወቀ ነው።

## ፪.፪ ከእሑድ እስከ አርብ ያሉ ፍጥረታት

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ የፈጸመው በስድስት ቀን ሲሆን በሰባተኛው ቀን ከመፍጠር አርፏል። በእነዚህ ስድስት ቀናት እግዚአብሔር የሚከተሉትን ሃያ ሁለት ፍጥረታት ፈጥሯል። ሃያ ሁለቱን ፍጥረታትንም በሦስት መንገድ ፈጥሯቸዋል።

**፩ኛ በነቢብ /በመናገር/ ይሁን በማለት/ ፡-** እግዚአብሔር በመናገር የፈጠራቸው ፍጥረታት አሥራ አራት ሲሆኑ እነርሱም

| | | |
|---|---|---|
| ብርሃን | ጠፈር | አዝርዕት |
| አትክልት | ዕፀዋት | ፀሐይ |
| ጨረቃ | ከዋክብት | ከባህር የተገኙት የሚሳቡት |
| | | የሚሽከረከሩት |
| | | የሚበሩት፣ |

ከምድር የተፈጠሩት የሚሳቡት

የሚሽከረከሩት


የሚበሩት ናቸው።

**፯ኛ በአርምሞ/ሳይናገር/፡-** ሰባት ፍጥረታት እነርሱም ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃ፣ መሬት፣ ጨለማ፣ ሰማያት፣መላእክት ናቸው፡፡

**፩ኛ በገቢር /በእጁ በመሥራት/፡-** አንድ ፍጥረት ሲሆን እርሱም የሰው ልጅ ነው፡፡

በ፩ኛው ቀን ዕለተ እሑድ የተፈጠሩ ፍጥረታት

በዕለተ እሑድ አምላካችን ስምንት ፍጥረትን ፈጥሯል፡፡




ሥዕል ፯.፯ ፡ የዕለተ እሑድ ሥነ ፍጥረት


👉ነፋስ፣ መሬት፣ እሳትና ውኃ አራቱ ባሕርያተ ሥጋ እየተባሉ ይጠራሉ፡፡

ልጆች ሰባቱ ሰማያት የሚባሉት

| | |
|---|---|
| ጽርሐ አርያም | መንበረ መንግሥት |
| ሰማይ ውዱድ | ኢየሩሳሌም ሰማያዊት |
| ኢዮር | ኤረር |
| ራማ ናቸው:: | |

## በ፪ኛው ቀን በዕለተ ሰኞ የተፈጠረው ፍጡር


ከመሬት ሆነን ወደላይ አቅንተን የምናየውን (በተለምዶ ሰማይ ብለን የምንጠራው) ጠፈር በሁለተኛው ቀን በዕለተ ሰኞ ተፈጥሯል::




ሥዕል ፪.፫፡ የዕለተ ሰኞ ፍጥረት ጠፈር (ሰማይ)

## በ፫ኛው ቀን በዕለተ ማክሰኞ የተፈጠሩት ፍጥረታት

እግዚአብሔር በዚህ ዕለት በመጥረቢያ የሚቆረጡ፣ በማጭድ የሚታጨዱ፣ በእጅ የሚለቀሙ ሦስት ፍጥረታትን ፈጥሯል:: እነዚህም ዕፀዋት ፥ አዝርዕት እና አትክልት ተብለው ይለያሉ::





ዕፀዋት　　　　　　አትክልት　　　　　　አዝርዕት

ሥዕል ፪ ፬፡ የዕለተ ማክሰኞ ፍጥረታት

## በ፬ኛው ቀን ዕለተ ረቡዕ የተፈጠሩት ፍጥረታት

በአራተኛው ዕለት እግዚአብሔር ሦስት ፍጥረታትን ፈጥሯል። እነርሱም ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ናቸው። የእነዚህም ተግባር በቀንና በማታ ብርሃንን መስጠት ነው።




ሥዕል ፪.፭፡ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት

## በ፭ኛው ቀን ዕለተ ሐሙስ የተፈጠሩት ፍጥረታት

በአምስተኛ ቀን በዕለተ ሐሙስ በውኃ ውስጥ የሚኖሩ ሦስት ፍጥረታት ተፈጥረዋል፡፡ እነርሱም

- በእግር የሚሽከረከሩ
- በክንፍ የሚበሩ
- በልብ የሚሳቡ
- እኒህም ሁሉ በባሕር የሚኖሩ ናቸው፡፡



ሥዕል ፱.፮ ፡ የዕለተ ሐሙስ ሥነ ፍጥረታት

## በ፮ኛው ቀን ዕለተ ዓርብ የተፈጠሩት ፍጥረታት

በመጨረሻው ቀን በዕለተ ዓርብ ፥ በየብስ (በምድር) የሚኖሩ አራት ፍጥረታት ተፈጥረዋል፡፡

- በእግር የሚሽከረከሩ
- በክንፍ የሚበሩ (አእዋፋት)
- በልብ የሚሳቡ እና
- በመጨረሻም ሰው ተፈጥሯል



ሀ. በእግራቸው የሚሽከርከሩ



ለ. በክንፋቸው የሚበሩ



ሐ. በደረታቸው የሚሳቡ

ሥዕል ፡ በዕለተ ዓርብ የተፈጠሩት ፍጥረታት

በ፯ ኛው ቀን  በዕለተ ቅዳሜ እግዚአብሔር ፈጥሮ ፈፅሞ ከሥራው አርፏል።ይህም እግዚአብሔር ሠርቶ የሚደክመው ሆኖ ሳይሆን ለሰው ልጆች ዕለተ ሰንበትን  ሊያከብሯት የሚገባ መሆኑን ለማሳየት፥ ለማስተማር ነው።

## ፪.፬ የሰው ልጅ ክቡር ፍጥረት መሆኑ

የሰው ልጅ በስድስተኛው ዕለት የፍጥረት መጨረሻ ሆኖ ተፈጥሯል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በመልኩና በአርአያው አድርጎ ከምድር አፈር አበጅቶ የሕይወትን እስትንፋስ አሳድሮበታል። እግዚአብሔር ሰውን ብቻ በግብር (በእጁ ሥራ) ፈጥሮታል። ምድርን፣ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ እንዲገዛ ሆኗል። የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ስለተጠራ እና ከላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች የሰው ልጅ ክቡር ፍጡር ይባላል።

### ተግባር

ልጆች እግዚአብሔር በስድስቱም ቀን የፈጠራቸውን ፍጥረታት በቃላችሁ በመያዝ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

፩. እግዚአብሔር ከሥነ ፍጥረት ሁሉ አንደኛ የፈጠረው የሰውን ልጅ ነው።

፪. ሥነ ፍጥረት ማለት ያማረ፣ የተዋበ የተወደደ ፍጥረት ማለት ነው።

፫. እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በአምስት መንገድ ፈጥሯቸዋል።

፬. እግዚአብሔር በዕለተ ረቡዕ ፀሐይ፣ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ።

በ "ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ለ" ሥር ካሉት ጋር ተስማሚያቸውን በመስመር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. በዕለተ ዓርብ የተፈጠረ | ሀ. ጽርሐ አርያም |
| ፪. ከሰባቱ ሰማያት መካከል አንዱ | ለ. ጠፈር |
| ፫. በእለተ ሰኞ የተፈጠረ | ሐ. ዛፍ |
| ፬. በእለተ ማክሰኞ የተፈጠረ | መ. ሰው |



# በቃል የሚጠና ጥቅስ

“እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር።”

(ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፮)

# ምዕራፍ ሦስት

## እግዚአብሔር መልካምን ነገር ሁሉ የሚሰጠንና ጸሎትን የሚሰማ ስለ መሆኑ

### የምዕራፉ ዓላማ

ልጆች ይህንን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ:

- በጸሎት ስለሚገኝ መልካም ነገርና እግዚአብሔር እንዴት ክክፉ ነገር እንደሚጠብቀን ያውቃሉ።

### ቁልፍ ቃላት

- ጸሎት : ምስጋና፣ ልመና፣ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ማለት ነው።
- ሥላሴ : ሦስትነት ወይም ሦስት መሆን ማለት ነው።

## ፫.፩ እግዚአብሔር መልካም ነገርን ይሰጠናል

- "እግዚአብሔር መልካም ነው" (ትንቢተ ናሆም ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፯) ስለዚህም በጎውን፣ መልካሙን፣ ለእኛ የሚበጀውን ሁሉ ይሰጠናል።

እግዚአብሔር መልካም እንደሆነ እኛን ከመፍጠሩ በፊት ለእኛ የሚያስፈልጉንንና ጥሩ የሆኑ ነገሮችን በማዘጋጀቱ እናውቃለን፡፡ ሲጠማን የምንጠጣውን ውኃ፤ ሲርበን የምንበላውን ምግብ ከአትክልቱም፣ ከእንስሳቱም፣ ከማሩም አዘጋጅቶልናል፤ ሲበርደን የምንለብሰውን ከእንስሳት ቆዳ እንድንሠራ አስተምሮናል፡፡

የምንጠለልበትን ቤት እንደ ገነት ያለ ቦታ ከዚያ ከወጣን በኋላ ለምንቆይበት ከዛፎች፣ ከሳሮች፣ ከአፈር፣ ከጡብ፣ ከድንጋይ ወይም በዋሻ የምናድርበትን እንድናዘጋጅም ፈጥሮልናል፡፡

በብቸኝነት እንዳንኖርም ረዳትን ማለትም ለአዳም ሐዋንን ለሔዋን ደግሞ አዳምን ፈጥሯል፡፡

- እንዲሁም ለተፈጠርንበት ዓላማ ከኖርንና ለእግዚአብሔር ከታዘዝን እግዚአብሔር መልካም የሆነን መልካም ነገርን ይሰጠናል፡፡ አምላካችን እግዚአብሔር እንዲህ ይለናል፡፡ "በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን የሆነውን ነገር ስታደርግ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ ለዘላለም መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ እኔ የማዝዝህን እነዚህን ቃሎች ሁሉ ሰምተህ ጠብቅ" (ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፲፪ ቁጥር ፳፰)
- በተጨማሪም አምላካችን **"እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ ፥የምድርን በረከት ትበላላችሁ፡፡"** በማለት ትናግሯል፡፡ (ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፲፱) ስለዚህ ልጆች እግዚአብሔር መልካም ነገርን እንዲያደርግልን ለእርሱ ልንታዘዝ ይገባል፡፡

## ፪.፪ እግዚአብሔር ጸሎትን ይሰማል

- ጸሎት ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ምስጋና እና ልመና ነው:: እኛ የሰው ልጆች እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናናግረው፥ እንደምናመሰግነው እንደምንለምነውም ሲያስተምረን እንዲህ ብሎናል:: **"ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፥ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ..."** (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ ቁጥር ፪)

- ስንጸልይና ከእግዚአብሔር ጋር ስንነጋገር እንደ ፈቃዱ መሆን ይገባል:: በእምነት ሆነን የምንጠይቀውን መልካም ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይሰጠናል:: "በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?" (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፲፩) ይለናል:: ስለዚህም እንዲህ ብሎ ቃል ገብቶልናል **"እናንተም ትጠሩኛላችሁ፥ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ ፥ እኔም እሰማችኋለሁ:: እናንተ ትሹኛላችሁ ፥ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ::"** (ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ ፳፱ ከቁጥር ፲፪ እስከ ፲፫)

- በመሆኑም እኛ ሕፃናት ማታ ስንተኛ፣ ጠዋት ስንነሳ፣ ከመመገባችን በፊት ልንጸልይ ይገባል:: እግዚአብሔር የሕፃናትንም የአዋቂዎችን ጸሎት ይሰማል:: የሠለስቱ ደቂቅ (የሦስቱ ልጆችን) ጸሎት ሰምቷል፣ እንዲሁም የሁሉንም ጸሎት ይሰማል:: ይሚፈልጉትንም መልካም ነገርም ያደርግላቸዋል::



ሥዕል ፫.፩ ሕፃናት ከመመገባቸው በፊት ጸሎት ሲጸልዩ

## ፫.፫ ስለ ክፋትና እግዚአብሔር ከክፉ ነገር የሚጠብቀን ስለመሆኑ

### ፫.፫.፩ የሰይጣን ክፋት

- ልጆች እግዚአብሔር ሳጥናኤልን ፈጥሮ ከመላእክት ጋር እንዲያገለግል ክብር ሰጥቶት የመላእክት አለቃ አድርጎት ነበር፡፡
- ይሁን እንጂ በመጀመሪያ የሰይጣን ክፋት የታወቀው የተሰጠውን ኃላፊነት ትቶ እኔ እግዚአብሔር ነኝ በማለት የውሸት ወሬ በማውራቱና ሌሎች መላእክትን ለማሳሳት በመሞከሩ ምክንያት እግዚአብሔር ከሥልጣኑ ሻረው፡፡ ስሙም ሰይጣን ተባለ፡፡ ከዛ ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን ውሸታም ሆነ፡፡

👉ሰይጣን ከወደቀ (ከተጣለም) በኋላ በምትኩ የተፈጠሩት አዳምና ሔዋን ላይ ቀናባቸው:: የሐሰት (የውሸት) አባት ነውና በእባብ ገላ (ሰውነት) ተሰውሮ በሐሰት አታልሎ ከእግዚአብሔር ይጣሉ ዘንድ የፈጣሪን ትእዛዝ እንዲጥሱ አደረጋቸው:: ጌታችን በወንጌል ስለ ሰይጣን ውሸታምነት ሲናገር እንዲህ ይላል፦ **“እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም:: ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና”** (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፵፬)

👉በመሆኑም አዳምና ሔዋንን ዋሽቶ አሳታቸው ለሞትም ዳረጋቸው:: ሰይጣን እነርሱን ብቻ አልፈተነም ራሱ ጌታችንን፣ ጻድቁ ኢዮብን፣ ቅዱስ ጳውሎስንም ሌሎችንም ፈትኗል:: ሌሎችንም የብርሃን መልአክ እየመሰለ ሊፈታተን እንደሚሞክር ተጽፏል:: **“ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል”** (ሁለተኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ዐሥራ አንድ ቁጥር ዐሥራ አራት)




ሥዕል ፫.፬ ፡ አዳምና ሔዋንን ስይጣን በእባብ አድሮ ሲያስታቸው

👉ሰይጣን ውሸታምና ክፉ የሰው ልጆችን የሚፈታተናቸው ቢሆንም እኛ ክርስቲያኖች ሁል ጊዜ በሚገባ ስንጸልይ እግዚአብሔር አምላካችን ይጠብቀናል።

## ፫.፬ ሥላሴ የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ



ሥዕል ፫.፫ እግዚአ ዓለማት ቅድስት ሥላሴ

👉እግዚአብሔር ከሚጠራባቸው ስሞች መካከል ሥላሴ የሚለው ስም አንዱ ነው። ይህ ቃል ሠለሰ ሦስት አደረገ ከሚለው የግእዝ ግስ የሚወጣ ስም ሲሆን ትርጉሙም ሦስትነት ወይም ሦስት መሆን ማለት ነው። የሚያመለክተውም የእግዚአብሔርን አንድ ሲሆን ሦስት መሆኑን ነው። መጽሐፍ ቅዱስም (በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ቍጥር ሃያ ስድስት ላይ) "እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር።" በማለት ሥላሴ አንድ መሆኑን ሲነግረን "እግዚአብሔርም አለ" ሲል "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር" በማለት ሦስትነቱን ነግሮናል።

👉ስለዚህ ሥላሴ የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ ስም ነው።

## ተግባር

### ነገረ ሥላሴን ለመረዳት የሚከተለውን ጥያቄና መልስ በደንብ አጥኑና በክፍል ውስጥ ልምምድ አድርጉ።

ጥያቄ "ማን ፈጠረህ?"

መልስ "ሥላሴ"

ጥያቄ "ሥላሴ ስንት ናቸው?"

መልስ "አንድም ሦስትም ናቸው።"

ጥያቄ "አንድነታቸው እንደምን ነው?"

መልስ "በመለኮት፣ በመንግሥት፣ በአገዛዝ፣ በፈቃድ፣ በመፍጠር፣ በህልውና እና በመሳሰሉት ሁሉ አንድ ናቸው"

ጥያቄ "ሦስትነታቸውስ?"

መልስ "በስም፥ በአካል፥ በግብር ሦስት ናቸው"

- በስም "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ"
- በአካል "አብ የተለየ አካል፥ ወልድ የተለየ አካል ፥መንፈስ ቅዱስ የተለየ አካል አላቸው"
- በግብር "አብ አባት ነው ይወልዳል ያሰርጻል፣ ወልድ (ልጅ) ይወለዳል፣ መንፈስ ቅዱስ ይሰርጻል"

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን “እውነት” ትክክል ያልሆነውን ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፡፡

፩. ሰይጣን ሐሰትን የሚናገር የሐሰት አባት ነው፡፡

፪. እግዚአብሔር የሰዎችን ጸሎት የሚሰማ አምላክ ነው፡፡

፫. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መልካም የሆኑ ነገሮችን ይሰጣል፡፡

፬. ሰይጣን እውነት ተናግሮ ያውቃል፡፡

፭. እግዚአብሔር ከሚጠራባቸው ስሞች መካከል ሥላሴ የሚለው ስም አንዱ ነው፡፡



## በቃል የሚጠና ጥቅስ

“እግዚአብሔር ጠባቂዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ፤”

(ሁለተኛ ሳሙኤል ምዕራፍ ሃያ ሁለት ቁጥር ሦስት)–

# ምዕራፍ አራት
# የእግዚአብሔር ባሕርይ

## የምዕራፉ ዓላማ

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ሲያጠናቅቁ፡

- የእግዚአብሔር ባሕርያት ምን ምን እንድሆኑ ያውቃሉ።

## ቁልፍ ቃላት

- ቅዱስ ፡ የተለየ ፣ የከበረ ማለት ነው።
- ሕያው ፡ ለዘላለም የሚኖር በሕይወት ያለ

ልጆች የእግዚአብሔር ባሕርይ በሰው ለጆች እወቀት መጠን የሚመረመር አይደለም። ነገረ ግን እኛ አመላካችንን ለማወቅ ስለ እግዚአብሔር ምንነት አባቶቻችን ባስተማሩን መሠረት የምንረዳበት መንገድ ነው። ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ከምናውቅበት መንገድ መካከል ቅዱስ ነው ፣ ሕያው ነው፣ በሁሉ ቦታ አለ ፣ ሰዎችን ሁሉ የሚወድ ነው እና ጸሎትን የሚሰማ ነው የሚሉትን በመጠኑ እንመለከታልን።

# የእግዚአብሔር ባሕርይ

## ፬.፩ ቅዱስ ነው

👉ቅዱስ ማለት የተለየ፣ የከበረ፣ንጹሕ የሆነ ማለት ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። **"እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና"** (ኦሪት ዘሌዋውያን ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፪ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስንል እግዚአብሔር የተለየ ነው፣ እግዚአብሔር የከበረ ነው፣ እግዚአብሔር ንጹሕ ነው እያልን ነው።

## ፬.፪ ሕያው ነው

👉**"እግዚአብሔር ሕያው ነው።"** (መዝሙረ ዳዊት መዝሙር ፲፯ ቁጥር ፵፮) ሕያው ማለት በሕይወት ያለ ለዘላለም የሚኖር ማለት ነው። **"እግዚአብሔርም ሙሴን፦ «ያለና የሚኖር» እኔ ነኝ አለው"** (ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፲፬) ሌላው እርሱ ሕያው ሆኖ ለሌላው ፍጥረት ሕይወትን የሚሰጥ ነው ማለት ነው።

## ፬.፫ በሁሉ ቦታ አለ

👉ሌላው የእግዚአብሔር ባሕርይ በሁሉ ቦታ መኖሩ ነው። እርሱ አምላክ ነውና በጊዜና ቦታ አይወሰንም። እዚህ ቦታ አለ እዚህ ቦታ ደግሞ የለም አይባልለትም። የሌለበት ቦታ የለምና። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ እያለ ይዘምራል። **"ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ አንተ ከዚያ አለህ።"**

## ፬.፬ ሰዎችን ሁሉ የሚወድ ነው

👉እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ይወዳል፡፡ ለዚህም ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው አድርጎ አክብሮ ፈጥሮታል፡፡ **“እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፡፡”** (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፳፮)

👉ሕፃናትንም እግዚአብሔር በጣም ስለሚወዳቸው ወደ እርሱ እንዲመጡ ይፈልጋል፤ የሚከለክሏቸውንም ይወቅሳል፡፡ አምላካችን እንዲህ በማለት ተናግሯል፡፡ **“ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ፦ ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና፡፡”** (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፲፬)



ሥዕል ፬.፩ ፡ ጌታችን ከሕፃናት ጋር

## ፬..፰ ጸሎትን የሚሰማ ነው

- ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ጸሎትን ይሰማል። ለዚህም ነው ፈልጉ ታገኛላችሁ እሹ ይሰጣችኋል አንኳኩ ይከፈትላችኋል ያለን።

- **"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።"** (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፯ ቁጥር ፯)

- ስለዚህ እኛ ልጆች በየዕለቱ በጸሎት ልናመሰግነው ይገባል።

### ተግባር

ልጆች ከላይ ያየናቸውን አምስት የእግዚአብሔር ባሕርያትን በቃላችሁ ከያዛችሁ በኋላ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተለማምዳችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።

## የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በትክክል ካነበባችሁ በኂላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

፩. እግዚአብሔር ሕፃናት ወደ እርሱ እንዲመጡ ይፈልጋል።

፪. ቅዱስ ማለት የተለየ፣ የከበረ፣ንጹሕ የሆነ ማለት ነው።

፫ ሕያው ማለት በሕይወት ያለ ለዘላለም የሚኖር ማለት ነው።

በ "ሀ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ለ" ሥር ካሉት ጋር ተስማሚያቸውን በመስመር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩. ዘውትር ልናደርገው የሚገባ | ሀ. እግዚአብሔር |
| ፪. የተለየ፣ የከበረ | ለ. ሕያው |
| ፫. በሕይወት ያለ ለዘላለም የሚኖር | ሐ. ቅዱስ |
| ፬. በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ | መ. ጸሎት |
| ፭.በሁሉም ቦታ ያለ | ሠ. ሰው |



# በቃል የሚጠና ጥቅስ

“ሕፃናትን ተዉአቸው ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና።”

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፱ ቁጥር ፲፬)